# 21 DAYS

## የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አማኞች ቤተክርስቲያን

# የጾምና ጸሎት ጥሪ



እግዚአብሔር ሆይ፤ የሥርዐትህን መንገድ አስተምረኝ፤
እኔም እስከ መጨረሻው እጠብቀዋለሁ።
ሕግህን እንድጠብቅ፣ በፍጹም ልቤም እንድታዘዘው፣
ማስተዋልን ስጠኝ። በእርሷ ደስ ይለኛልና፣
በትእዛዝህ መንገድ ምራኝ።
(መዝ119:33-35)

- ማለዳ በስልክ ከ5፡30 am– 7፡00 am
- 848.777.1212 Code 55064#

## ከDecember 2 – December 22, 2024

ከሰኞ -አርብ ማለዳ በስልክ 5፡30am- 7፡00 am
ቅዳሜ ማለዳ በአካል 7፡00Am-8፡30Am Morgan Chapel
እሁድ ማለዳ. በአካል 9፡15 am -10፡15 am

ከሰኞ-እሁድ ማታ በአካል በቤተክርስቲያን
6፡30Pm- 8፡00 Pm Morgan Chapel

## *ፆም ና ጸሎት በአማኝ ህይወት!!*

በጸጋ መዳናቸውን አስደግፈው መጾምን በተመለከተ “አያስፈልገንም” የሚሉ አሉ ። ሌሎች ደግሞ ወደ ጌታ መቅረቢያ ሥራቸው አድርገው “ያስፈልጋል” ይላሉ። የሁለቱም ወገኖች ዕይታ ጽንፈኛነት አለው። በመሰረቱ ብዙ የእግዚአብሔር ወዳጆችና አገልጋዩች ጾመዋል። የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ 40 ቀናት(ዘጸ34፡28) ፥ ንጉሡ ዳዊት 7 ቀናት(2ሳሙ12፡16-18)፥ ንግሥት አስቴር 3 ቀናት( መጽ.አስ 4፡16)፥ ሐዋርያው ጳውሎስ 3 ቀናት( ሐዋ9፡9)፥ እሥራኤል 1 ቀን(ነህ 9፡9) መጾማቸውን ለአብነት ያህል ከቃሉ ማየት ይቻላል።

መጾምን እንደሃይማኖተኝነት ሥራ አድረገን የምንመካበት ከሆነ በጌታ ዘንድ ተቀባይነት ከማጣቱም በላይ ዕዳ የሚያመጣ ይሆናል። ትህትና የለበትምና።

- **ለታይታ አይሁን!!!** “ስትጦሙም፥ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤ ለሰዎች እንደ ጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፋሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጦም፥ በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ ፊትህንም ታጠብ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።” ማቴ. 6፡ 16-18
- **ጾም ና ጸሎት እግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት።** እርሱን ለመፈለግ፥ እርሱን ለማምለክ ና ለእርሱ ፈቃድ ለመገዛት። ነቢይቷ ሐና “በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር” (ሉቃ. 2፡ 37)። በአንጾኪያም የነበሩት ያደርጉት ይህንኑ ነበር። “ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ፣ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ” ( ሐዋ. 13፡ 2)። በነቢዩ ዘካሪያስ የመጣው መልዕክት ይህ ነበር። እንዲህ ሲል “ለምድሩ ሕዝብ ሁሉ ለካህናትም እንዲህ ብለህ ተናገራቸው። በዚህ በሰባው ዓመት በአምስተኛውና በሰባተኛው ወር በጾማችሁና ባለቀሳችሁ ጊዜ፥ በውኑ ለእኔ ጾም ጾማችሁልኝ?” (ዘካ.7፡ 5) ለጌታ ና ወደ ጌታ ካልጾምን ከንቱ ይሆንብናል።
- **በጾምን ቀን ፈቃዱን ለማድረግ እንትጋ** “ስለ ምን ጾምን፥ አንተም አልተመለከትሽንም? ሰውነታችንንስ ስለ ምን አዋረድን፥ አንተም አላወቅህም? ይላሉ። እነሆ፥ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ፥ . . . በውኑ ይህን ጾም፥ በእግዚአብሔርም ዘንድ የተወደደ ቀን ትለዋለህን? . . .” ትን. ኢሳ. 58፡ 1-14 እንግዲያስ በጾምን ቀን እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ሌሎችን የሚጠቅመውን ሁሉ እናድርግ። ያን ጊዜ እግዚአብሔርም ይሰማናል እርሱም፡- እነሆኝ ይለናል።
- **ስለ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ጾም ና ጸሎት ይደረጋል፤ ጌታም እጁን ልኮ ይረዳል።** በጦርነት ጊዜ ለድል (2 ዜና 20), በበደል ለንስሃ (ዮናስ 1-4), በጉዞ ላይ ለጥበቃ (ዕዝራ 8), አጋንንትን በኃይል እንዲወጡ ለማድረግ (ማቴ. 17), ትልልቅ ችግሮች በቤተሰብ፤ በቤተክርስቲያንም ሆነ በሀገር ደረጃ ለመፍታት ጾምና ጸሎት ይደረጋል። ጌታም ታምራትን ያደርጋል።

**ግንዛቤ፡-** መጾም የተለያየ መንገድ አለው። ከምግብ ና ከውኃ በመለየት (ዘዳ.9፡9) ፥ ቅባት ካለበት ማለፊያ ምግብ በመቆጠብ (ዳን. 10፡3) ። ሰውነታችን በፍጥረቱ ያለ ውኃ ለመቆየት ስለሚከብደው ረዥም ቀናት ጾም ከምግብ ተለይቶ ውኃ እየወሰዱ ይደረጋል።

ለረዥም ቀናት በተከታታይ የሚወሰዱ የጾም ቀናትን መጨረስ በሚፈለግበት ጊዜ ለጤንነት እንቅፋት እንዳይሆን ከሚጠጡ ፈሳሾች ጀምሮ ወደ ሚታኘኩ ምግቦች የመሸጋገር ብልሃት አስፈላጊ ነው።

ትን. ዘካ. 8፡ 19 “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- የአራተኛው ወር ጾም የአምስተኛውም የሰባተኛውም የአሥረኛውም ወር ጾም ለይሁዳ ቤት ደስታና ተድላ የሐሤትም በዓላት ይሆናል . . .” **ይሆናል**

**የየዕለቱ ንባብ ክፍል**

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2-Dec | ሉቃስ1-2 | | 9-Dec | ሉቃስ 10 | | 16-Dec | ሉቃስ 18 | |
| 3-Dec | ሉቃስ 3-4 | | 10-Dec | ሉቃስ 11 | | 17-Dec | ሉቃስ 19 | |
| 4-Dec | ሉቃስ 5 | | 11-Dec | ሉቃስ 12 | | 18-Dec | ሉቃስ 20 | |
| 5-Dec | ሉቃስ 6 | | 12-Dec | ሉቃስ 13 | | 19-Dec | ሉቃስ 21 | |
| 6-Dec | ሉቃስ 7 | | 13-Dec | ሉቃስ 14 | | 20-Dec | ሉቃስ 22 | |
| 7-Dec | ሉቃስ 8 | | 14-Dec | ሉቃስ 15-16 | | 21-Dec | ሉቃስ 23 | |
| 8-Dec | ሉቃስ 9 | | 15-Dec | ሉቃስ 17 | | 22-Dec | ሉቃስ 24 | |

**ቀን -ሰኞ December 2 2024**

**ፈተና (temptation)**

**ዘፍ3፥1-7**

**እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ። ሴቲቱንም፦ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት።ሴቲቱም ለእባቡ አለችው፦ በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን፤ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ፥ እግዚአብሔር አለ፦ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም።እባብም ለሴቲቱ አላት፦ ሞትን አትሞቱም፤ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ። ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች፤ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ።የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፥ እነርሱም ዕራቁታቸውን እንደ ሆኑ አወቁ፤ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ።**

***ማብራሪያ***

**እግዚአብሔር ሰውን በመልኩና በምሳሌው ፈጥሮ ለክብርና ለበረከት እንዲሆን ቢያደርገውም፤ ሰው ከእግዚአብሔር ህብረት እንዴት ሰይጣን እንዲወጣ እንዳደረገው ስንመለከት ሶስት ነገሮችን እንገነዘባለን።**

- **በማታለል የሔዋንን አሳብ ማበላሸቱ**
- **በተበላሸ አሳብ ወደ አለመታዘዝ ማምጣቱ**
- **በአለመታዘዝ ከእግዚአብሔር አገዛዝ ወጥቶ ራስን ወደ ማስተዳደር ፍላጎት ማዘንበሉ**

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ**

1. **የሰይጣንን የመጀመሪያ የጥቃት ትኩረቱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ህብረት ነው። ይህንንም የሚያስፈጽመው ስለአምላካችን ያለንን አሳብ በማበላሸት ነው ።ጌታ አሳባችንን እንደቃሉ እንዲያቀናልን እንጸልያለን።**
2. **የአለመታዘዝ ህይወት ከብዙ በጎነት የሚያጎድል ሲሆን ጌታ ከዚህ እንዲጠብቀን እንጸልያለን።**
3. **አመጸኝነት የእግዚአብሔርን ባህሪ ስለማይገልጥ በጌታ ፊት በመታዘዝ ልብና መንፈስ እንድንመላለስ ጸጋ እንለምናለን።**

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች**

1. **አንዱ በቤተክርስቲያን ሰይጣን ህብረትን የሚጎዳበት መንገዱ የቃሉን ስልጣን ስሜት የሚሰጡ በሚመስሉ አሳቦች መተካት ሲሆን ጌታ እኛን ከዚህ ስንፍና እንዲጠብቀን እንጸልያለን**
2. **ነጻነት በሚመስል በቤተክርስቲያን እግዚአብሔር ያስቀመጣቸውን መሪዎችን አለመስማትና ፤ ሁሉም በፊቱ መልካም የመሰለውን መናገርና የማድረግ በበዛበት በዚህ ዘመን ጌታ አካሉ በስርዓት እንዲመራ የሰጠንን መሪዎች መስማትና ማክበር እንዲሆንልን እንጸልያለን**

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- **ለቤተክርስቲያ የሽማግሌ ጉባኤ እንጸልያለን**

**የግል ወይም ስለ ሌሎች የምንጠይቃቸው የጸሎት ርዕሶች**

**1.____________________________________________**

**ቀን - ማክሰኞ December 3 2024**

**ውድቀትና ውጤቱ (fall of man)**

**ዘፍ3፥14-19&ሮሜ5፥12**

እግዚአብሔር አምላክም እባቡን አለው፦ ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ትሆናለህ፤ በሆድህም ትሄዳለህ፥ አፈርንም በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ትበላለህ።በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።ለሴቲቱም አለ፦ በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፥ እርሱም ገዥሽ ይሆናል።አዳምንም አለው፦ የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና፥ ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ፤ እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ።ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ አፈር ነህና፥ ወደ አፈርም ትመለሳለህና።
።" ዘፍ3፡14-19

**ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤ሮሜ5፥12**

***ማብራሪያ***

**እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ፈጥሮ በኤደን ካስቀመጠው በዋላ እንዲበላ የሰጠው እና እንዳይበላ የከለከለው እንደነበረና ፣ሆኖም የከለከለውን ባለመታዘዝ ቢበላ የሚደርስበትን ቀድሞ እንደነገረው ፣በበላ ጊዜ ወደ ዓለም ሞትና አጢያት እንደገባ መጽሐፉ ያስተምረናል**

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ**

1. **ሰው እግዚአብሔር በሰጠው ክብር ውስጥ እንዳይኖር ያደረገው የመውደቁ ምክንያት በአለመታዘዝ ጠንቅ ነው።**
    1. **አለመታዘዝ ያመጣውን ውድቀት በአዳምና በሔዋን የተመለከትን ሲሆን ይህንን እያሰብን ቅዱሳን ከውድቀት ይጠበቁ ዘንድ እግዚአብሔር በቃሉ ያሰመረውን መስመር እንዳንተላለፍ እንጸልያለን**
    2. **የአዳምና የሔዋን መተላለፍ ከእነርሱ አልፋው ለሰው ልጅ ሁሉ እንደሆነ እንዲሁ ሞትና የሞት ህግ ወደ ዓለም እንደገባ ሁሉ ፣እኛም ውሳኔዎችቻን እንድናስተውል ጌታ እንዲረዳን እንጸልያለን ።**

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች**

- **ቤተክርስቲያን በምድር ላይ በትክክል ተልዕኮዋን ስትፈጽም ለምድር በረከት ትሆናለች የማይታዘዘውን ዓለም ወደ መታዘዝ እንዲመጣ ምልክት ትሆናለች። ጌታ የዳላስ ቤተክርስቲያን እንዲረዳ እንጸልያለን።**

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- **ለቤተክርስቲያን አገልጋዮች(staff) እና ቤታቸው እንጸልያለን**

**ቀን - ረቡዕ December, 4 2024**

**የዕለቱ የጸሎት ርዕስ ፡ - የመስቀሉ ስራ**

**ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ።እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና፥ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል።።** 1 **ጴጥሮስ** 2: 24-25

**ማብራሪያ**

በሃጢያት ምክንያት ሞት ተፈርዶብን ከእግዚአብሔር የተለየነውን ፣ተስፋ ቢስና ግራ የተጋባ ህይወት የነበረንን ጌታ የኛ ምትክ በመሆን የሃጢአታችንን እዳ በመስቀሉ ላይ ከፍሎ ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቆ ከሃጢአት ባርነት ነጻ አወጣን።የክርስቶስ መስቀል የነጻነታችን አርማችን (ምልክታችን)ነው።

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. እስራኤል በምድረበዳ በእባብ ተነድፎ ሳለ እግዚአብሔር የሚድኑበትን የነሐስ እባብ ሙሴ ሰርቶ ከፍ አድርጎ እንዲሰቅለው እንዳደረገና እርሱን ያየ ይፈወስ እንደነበረ ፣ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ መዳኛ ይሆን ዘንድ ለአመጽኛው ዓለም ምትክ ሆኖ ለሃጢአታችን የሚገባውን ዋጋ በመስቀል ላይ እንደከፈለ እያሰብን በብዙ ምስጋን እንጸልያለን ፡፤
2. መስቀሉ ከተገዛንበት ሃጢአትና በእርሱም ምክንያት ከመጣብን ዕዳ ነጻ የመውጣታችን ምልክት ነው፡፡ደግሞ በምንም ባርነት እንዳንያዝም የሚያሳስበን አሳታዋሻችንም ነው።

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. በክርስቶስ ቤተክርስቲያን መድረኮች ላይ የመስቀሉ ስራ ማዕከል ያደረጉ ትምህርቶች፣ስብከቶች እና ዝማሬዎች እንዲቆጣጠሩት እና ለዚህም ጌታ የአገልጋዮቹን አይን እንዲከፍት እንጸልያለን።
2. ጌታ ከክርስቶስ ቤተክርስቲያን መድረኮች ላይ መስቀል አልባ የሆኑ ስብከቶችን እንዲያስወግድ እንጸልያለን።

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- **የመጽሐፍ ቅዱስ ህብረትን እያሰብን እንጸልያለን**

**ቀን - ሐሙስ December, 5 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡ - የኢየሱስ ደም 1ጴጥ1፡17-19 & (ሮሜ 5፡9)**

**ለሰው ፊትም ሳያደላ በእያንዳንዱ ላይ እንደ ሥራው የሚፈርደውን አባት ብላችሁ ብትጠሩ በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ። ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን፥ ነውርና እድፍ እንደ ሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ።** (1ጴጥ1፡17-19)

ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቍጣው እንድናለን።(ሮሜ5፡9)

**ማብራሪያ**

**ከሃጢአት ባርነት ነጻ ወጥተን ከእግዚአብሔር ቁጣ አምልጠን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያገኘነው ከምንም በላይ ዋጋ ባለውና በከበረ እንዲሁም በንጹህና እንከን አልባ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም አማካኝነት ነው።**

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. **የኢየሱስ ደም የዋጀን አንዱ ከንቱ ከሆነው በውርስ ከተቀበልነው ህይወት ነው። ይህ ህይወት የውድቀት የእርግማንና ከእግዚአብሔር ውጪ የሆነ ነበር። አሁን ግን በቅዱስ ደሙ ዋጅቶናል። ክብር ለጌታ እየሰጠን እናመሰግናለን**
2. **ደሙ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንድናገኝ ከፍርድና ከቁጣ ነጻ እንድንሆን ፣ከጌታ ውጪ ማንም እንዳይገዛን የሆንበት ነው ።ለዚህም ጌታን እያመሰግንን እንጸልያለን።**
3. **በደሙ በኩል ያገኘነው ጽድቅ ከጠላት ክስ ነጻ የሆንበት ነውና ወንድሞችንና እህቶችን እየከሰሰ የደሙን ዋጋ የሚያሳንሰውን እየተቃወምን እንጸልያለን ፡፡**

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. **ቤተክርስቲያን የተመሰረተችው በዚሁ ደም ነው ። በዚህም ዘመን ባላደራ የሆኑ አገልጋዮች በደሙ የዋጃትን ቤተክርስቲያ እንደባለቤቱ ፈቃድ እንዲጠብቁ** (ሐዋ 20፡28-29)
2. **ቅዱሳን በቤተክርስቲያን ያለንን ህብረት ስናስብ የተዋጀንበትን ደም ማሰብና በዚያ ልክ ማክበር እንዲሆንልን እንጸልያለን**

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- **የኮኔክት**(connect ) **እና የእህቶችን አገልግሎትን ይዘን እንጸልያለን**

**ቀን** - ዓርብ December 6, 2024

**የዕለቱ ንባብ፡** - እምነት (ኤፌ2፡6-9)

**በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለ ጠግነት ያሳይ ዘንድ፥ ከእርሱ ጋር አስነሣን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን። ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።**

**ማብራሪያ**

**ከሞት ወደ ህይወት መሻገራችንን፣የእግዚአብሔር ልጅ መሆናችንን፣በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር መቀመጣችንን ስናስብ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ የሚገኘውን ድነት በነጻ አድሎናል። ይህን ክቡርና ውድ ስጦታ የተቀበለነው በእምነት በኩል እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል።**

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. የተቀበልነው ስጦታ(ህይወት፣ልጅነት፣በሰማያዊ ስፍራ መቀመጥን) ነጻ የሆነው ርካሽ ስለሆነ ሳይሆን ምንም ዋጋ ከፍለን የራሳችን ማድረግ የማንችል ስለሆነ ነውና ለዚህ ትልቅና የከበረ ስጦታ ጌታን እያመሰገንን እንጸልያለን።
2. ይህ ነጻ ስጦታ የተቀበልነው በስራ ሳይሆን በእምነት ነው። በእምነት የተቀበልነው እይወት እስከመጨረሻ በእምነት እንድንመላለስ ጌታ እንዲረዳን እንጸልያለን

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. **በቤተክርስቲያን በትምህርታችንም ሆነ በልምምዳችን በእምነት የዳንበት ወንጌል ብቻ የሚያንጸባርቅ እንዲሆን እንጸልያለን**
2. **እምነት ጌታ ያደርገውን ተከትለን እንድንኖር እንጂ ገደብ የሌለውን የእኛን ፍላጎት ማስፈጸሚያ ከሚመስል ትምህርት ቤተክርስቲያን እንድትጠበቅ እንጸልያለን**

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- **የድራማ እና ስነጽሑፍን አገልግሎት ይዘን እንጸልያለን**

**ቀን - ቅዳሜ December 7, 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡ - ጸጋ (ኤፌ 2፥8-9)**

ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።

**ማብራሪያ**

ጸጋ ለማይገባው ሰው የተሰጠን ውድ ስጦታ ነው። ይህ ማለት ያገኘነው ድነት የኛ የጽድቅ ስራ ውጤት ወይንም ከኛ ከሆነ የትኛውም ጥረት የተነሳ የመጣ አይደለም፤ይልቁንም እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ለሰው ልጆች
የገለጠው ፍቅር ፣ቸርንት እና ምህረት ውጤት ነው ።

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠውን ይህንን ድንቅ ጸጋ እያሰብን በምስጋና እንጸልያለን።
2. ከዚህ ጸጋ ውጪ መንፈሳዊ መሆን አይቻልምና ከዚህ ጸጋ ወድቀን እንዳንገኛ በዳንበት በዚያው ጸጋ መኖር እንድንችል እንጸልያለን።
3. ይህንን የዳንበትን ጸጋ ለሌላው ማካፈል እንችል ዘንድ ልባችንን ጌታ እንዲቀሰቅሰው እንጸልያለን።

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡**

1. በቤተክርስቲያን የጸጋ ወንጌል ትምህርት በሀይል ይሰበክ ዘንድ ጌታ ለባሪያዎቹ የቃሉን ፍቺ ያበራላቸው ዘንድ እንጸልያለን
2. እንዲሁም በጸጋ ትምህርት ሽፋን ቅዱሳንን ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ የህይወት ምልልስ የሚያበረታታውን የክፉውን ትምህርት እየተቃወምን እንጸልያለን።
3. በህግ መዳን ይቻላል የሚል ትምህርትና ልምምድ ውስጥ ያሉትን ጌታ ብርሃኑን እንዲልክ እና በጸጋ የመዳንን እውነት እንዲያበራላቸው እንጸልያለን

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- ❖ **የመስተንግዶን አገልግሎት ይዘን እንጸልያለን**

**ቀን - እሁድ December 8, 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡ - ንስሐ/መመለስ (ሐዋ 2፡36-38)**

እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ።
ይህንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ፥ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት፦ ወንድሞች ሆይ፥ ምን እናድርግ? አሉአቸው። ጴጥሮስም፦ ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።

**ማብራሪያ**

ንስሓ በክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ሐጢያታችን በመስቀል ላይ የተከፈለውን ዋጋ (ወንጌል) በመስማት እና በሐጢያታችን ተጸጽትን ወደ እግዚአብሔር ለመለስ መወሰን ነው።

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የተጣላውን ሰው ወደ ራሱ ይስበው ዘንድ የንስሐ መንገድ በኢየሱስ ክርስቶስ አዘጋጅቶለታል፣እኛም የዚህ ተካፋዮች ነንና እያመሰገንን እንጸልያለን
2. የንስሐ የገባ ሰው የእግዚአብሔርን ስጦታ የሆነውን መንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንዲቀበል ቃሉ እንደሚነግረን እንዲሁ እንዲሆንብን እንጸልያለን

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. ጌታ በመካከላችንም ሆነ በሚዲያ ከዚህች አጥቢያ ወንጌል ሰምተው ገና ምላሽ ያልሰጡ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳቸው እንጸልያለን።
2. በዚህ ከተማ ካሉ ብዙዎች ጌታ እንዲሰጠን በጉባያችንም በምንሰበሰብበት ሁሉ ንስሐ የሚገቡና ወደ ጌታ ዞር የሚሉ ብዙዎች እንዲመጡ እንጸልያለን።

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- **የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ይዘን እንጸልያለን**

**ቀን - ሰኞ December, 9 2024**

**ዕለቱ ንባብ፡ - ፦ ዳግም ውልደት (1ጴጥ 1፡23& ዮሐ1፡12)**

ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።(1ጴጥ1፡23)

**ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው። (ዮሐ1፡12)**

**ማብራሪያ**

**ሰዎች ሁሉ የተፈጠሩት በእግዚአብሔር ቢሆንም ለሰዎች ሁሉ ግን እግዚአብሔር አባት አይደለም ። የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት መቀበል ያስፈልጋል። ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት ተቀብሎ በመንፈስ ቅዱስ የሚደረግ ውልደት የዳግም ልደት ይባላል።**

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. **ዳግም የተወለድነው ተመልሶ ከማይበላሽና ከማይጠፋ ዘር እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል። ለዚህም ጌታን እያመሰገንን እንጸልያለን።**
2. **ከእግዚአብሔር ዳግም መወለዳችን የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንድንጠራ ስልጣን ሰጥቶናል ። ጌታ ዳግም መወለድ ሚስጥር እና ብርሃን እንዲያበራልን እንዲሁም የምንኖርበትን ጸጋ እንዲያበዛልን እንጸልያለን።**

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ --**

1. **ቤተክርስቲያን በምድር ያለችው ከእግዚአብሔር የተደረገውን የልጅነት ጥሪ ማድረስ ነው።በዚህ ጌታ የተጠሪዎቹን ጆሮና ልብ እንዲሰጠን እንጸርልያለን**
2. **መልካም በማድርግ የእግዚአብሔር ልጅነት እንደሚገኝ የሚመስላቸው እውነተኛውን ድምጽና መልዕክት ከቤተክርስቲያን ይደርሳቸው ዘንድ ጌታ እንዲረዳን እንጸልያለን**

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- ❖ **ለልጆች አገልግሎት ይዘን እንጸልያለን**

**ቀን - ማክሰኞ December 10, 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡ - መንፈሳዊ ዕድገት(ዕብ5፥11-14)**

ስለ እርሱም የምንናገረው ብዙ ነገር አለን፥ ጆሮቻችሁም ስለ ፈዘዙ በቃል ልንተረጕመው ጭንቅ ነው። ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፥ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም። ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለ ሆነ የጽድቅን ቃል አያውቅምና፤ ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በስራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው።

ማብራሪያ

የመንፈሳዊ ሕይወት እድገት በተፈጥሮ እንዳለ የሰው ልጅ እድገትን ይመስላል። ልጅ ከተወለደ በኋላ ከናት ጡት ወተት ጀምሮ ደረጃ በደረጃ እድገቱን የሚመጥን ምግብ እየተመገበ በሚመገበውም ምግብ አካሉ እና አእምሮው እየደረጀ ሀላፊነትን መቀበል ወደሚችልበት ሙሉ ሰው ወደመሆን ይደርሳል መንፈሳዊ ሕይወትም እንደዚሁ ነው ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን በዳግም ልደት የተጀመረ መንፈሳዊ ሕይወት ፣የእግዚአብሔር ቃልን ደረጃ በደረጃ እየተማርን በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ወደ ፍፅምና(ክርስቶስን ወደ መምሰል) እና መልካም የሆነውን የእግዚአብሔርን ስራ ለመስራት የምናድግበት እንደሆነ ከቃሉ እንረዳለን።

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. ፍጥረታዊ ሰው ከመወለዱ ጀምሮ ወደ ሙሉ ሰው እንደሚያድግ ሁሉ እንዲሁ ጌታን የተቀበለና ዳግም የተወለደ ሰው ክርስቶስን ወደ መምሰል ማድግ ይኖርበታል። ለዚህም ጌታ እንዲረዳን እንጸልያለን
2. በእግዚአብሔር ቤት በቆየንና በተማርን ቁጥር እንደ እድሜያችን እድገት የሚጠበቅብን ነውና ጌታ ወደ ጠንካራ ምግብ ፈቀቅ እንል ዘንድ ማስተዋልን እንዲሰጠን እንጸልያለን
3. መንፈሳዊ እድገት የሚገኘው ለቃሉ ፣ለህብረትና ለጸሎት ዳተኛ ባለመሆን ነውና ፣ ጌታ ዳተኝነትና ከእኛ ላይ እንዲያነሳ እንጸልያለን

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. እግዚአብሔር በክርስቶስ አካል በአምስቱ ቢሮ ውስጥ የሚያገለግሉትን ክፉንና መልካሙን የሚለዩበት ብስለትን እንዲያበዛላቸው እንጸልያለን።
2. በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ብስለት በማጣት ስለበዛው ስርዓት አልበኝነት በጌታ ፊት ንስሐ እየገባን ጌታ አካሉን እንዲያነቃት እና ለጊዜው የሚመጥን አቅጣጫ እንዲሰጣት እንጸልያለን

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- ❖ **ፓዝዌይ** (Pathway church)**ቤተክርስቲያንን አስበን እንጸልያለን**

**ቀን - ረቡዕ December 11, 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡ ህብረት(ዕብ10፡24-25)**

*ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው*

*እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።*

***ማብራሪያ***

*ድነት ያስገኘልን ትልቁ በረከት ከእግዚአብሔር እና ከቅዱሳን ጋር ሕብረት ማድረግ ነው። በመጨረሻው ዘመን ላለነው የእግዚአብሔር ቃል የሚያሳስበን ማንም ደክሞ ወደኋላ እንዳይቀር እርስ በእርሳችን በፍቅር ፣በመተሳሰብ ፣ በመረዳዳት እና በመበረታታት የጌታን መመለስ እንድንጠባበቅ ነው።*

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. *ቅዱሳን በህብረት እንዲኖሩ የጌታ አሳብ ነው ።የቅዱሳንን ህብረት የሰጠንን ጌታ እያመሰገንን እንጸልያለን*
2. *ዘመኑ እየተፈጸመ ባለበት ጊዜ የመሰባሰባችንን ልማድ እንዳንተው መጽሐፍ ቅዱስ ይመክረናል። በተለያዩ ምክንያት ከመሰባሰብ የጎደሉ ሰዎችን እያሰብን እንጸልያለን*
3. *የመሰባሰባችን ጥቅሙ በመንገድ እንዳንቀር ፣ሩጫውን እንድንጨርስ እርስ በእርሳችን እንድንበረታታ ነውና ፤ ይህ እንዳይሆን የሚታገለውን ክፉ እይተቃወምን እንጸልያለን*

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. *በቤተክርስቲያን ቅዱሳን ሁሉ በአካል ውስጥ እንደባይተዋር እንዳይወጡና እንዳይገቡ ይልቁንም በትናንሽ ህብረት ውስጥ እንዲሳተፉ ከቅዱሳን ጋር እንዲተሳሰሩ እንጸልያለን።*
2. *ህብረት አልባ የሆኑ በዚህ ከተማ ያሉ የጌታ ልጆች ያለእረኛ መሆን መልካም ስላልሆነ ጌታ ወደ ፈቃዱ እንዲመልሳቸው እንጸልያለን*

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- **የባንድ አገልግሎት አሰበን እንጸልያለን**

**ቀን - ሐሙስ December 12, 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡ - የጌታ ቃል 2ጢሞ 3፥14-17**

*አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፤ ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል። የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትናለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።*

**ማብራሪያ**

*መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በቅዱሳን ሰዎች ይሁን እንጂ የቃሉ ምንጭ መንፈስ ቅዱስ ነው የቃሉ ባለስልጣንነትም ከዚህ የተነሳ ነው። ስለሆነም እውነትን ለማስተማር የተሳሳቱትን ለመገሰጽ ስሕተትን ለማረም ብቃት አለው፡፡ ስለሆነም የእግዚአብሔር ቃል ፍጹም ወደመሆን እና ለመልካም ስራ ለመስራት የተዘጋጀን እንድንሆን እንደሚጠቅመን ቃሉ ይነግረናል።*

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. *የእግዚአብሔር ቃል ምንጩ መንፈስ ቅዱስ ነው።ዘመናችንን እንድንመራበት ስለተሰጠን የህይወት ቃል እያመሰገንን እንጸልያለን*
2. *የእግዚአብሔር ቃል የሚሰራውን ሁሉ በህይወታችን እንዲሰራ ቃሉን ማክበር እና እንደሚሰራ ማመን ይጠይቃል። ይህ የውስጥ ምስክርነት ወይንም እምነት በቅዱሳን ህይወት ላይ ገዢ እንዲሆን እንጸልያለን ።*
3. *የጌታ ቃል ከሁሉ በላይ ስልጣን ያለው ነውና በቅዱሳን ህይወት ላይ ከማንም ሰውና የሰው ሃሳብ በላይ እንዲሆን እንጸልያለን*
4. *ቅዱሳን በጌታ ቃል የታጠቁና የቃሉ ወዳጆች እንድንሆን እንጸልያለን*

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. *በቤተክርቲያን መድረኮች ላይ ሁሌም ንጹህ የሆነው የጌታ ቃል የተከፈተ እንዲሆን እንጸልያለን ።*
2. *በክርስቶስ አካል የእግዚአብሔር ቃል የሚያቃልል ሽልኮ የገባ የክፉ ስራ እየተቃወምን እንጸልያለን*

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- ❖ **የትምህርት ዝግጅት ክፍልን አስበን እንጸልያለን**

**ቀን - ዓርብ December 13, 2024**
**የዕለቱ ንባብ፡ - ጸሎት(ሉቃ18፡1-8)**

ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው የሚል ምሳሌን ነገራቸው፥እንዲህ ሲል፦ በአንዲት ከተማ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር አንድ ዳኛ ነበረ። በዚያችም ከተማ አንዲት መበለት ነበረች፥ ወደ እርሱም እየመጣች፦ ከባላጋራዬ ፍረድልኝ ትለው ነበር። አያሌ ቀንም አልወደደም፤ ከዚህ በኋላ ግን በልቡ፦ ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር፥ይህች መበለት ስለምታደክመኝ ሁልጊዜም እየመጣች እንዳታውከኝ እፈርድላታለሁ አለ። ጌታም አለ፦ ዓመፀኛው ዳኛ ያለውን ስሙ። እግዚአብሔር እንኪያስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ለሚታገሣቸውም ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን?እላችኋለሁ፥ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል። ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን?

**ማብራሪያ**

ጸሎት ከማናየው ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነው። እርግጠኛ ሆነን በጸሎት እንድንቀርብ የሚያስችለን እምነት ነው፡፡የምናምነው የእግዚአብሔርን ሁሉንቻይነት እና መልካምነት እንዲሁም ሊሰማንና ሊረዳን የሚወድና የሚፈቅድ መሆኑን ነው።

የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -

1. በዚህ ቅዱስና ታላቅ አምላክ ፊት ዘውትር በጸሎት እንድንቀርብ እድል ስለተሰጠን ጌታን እያመሰገንን እንጸልያለን።
2. በጌታ ፊት በጽሎት ከመቅረብ እንዳንታክት ጌታ በቃሉ አሳስቦናል ይህንንም እያሰብን ጌታ ልህዝቡ የሚጸልይበትን ፍላጎትና ትጋት እንዲጭምርልን እንጸልያለን።
3. ቅዱሳን በጌታ ፊት እንዳይጸልዩ የሚያደርገው አንዱ ጠላት ተስፋ በማስቆረጥ ነው። ይህንንም የሚያድርገው በእግዚአብሔር ባህሪ ላይ በመዋሸት ነው።

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. በቤተክርስቲያን የጸሎት ሃይል እንዲጨምር እንዲሁም በዚህ ውስጥ የሚገለጠው የሃይሉ ስራ እንዲበዛ እንጸልያለን።
2. በቅዱሳን ህብረቶች ውስጥ የሚደረጉ ጸሎቶች ቃል መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ እንጸልያለን።
3. ጌታ የምልጃን መንፈስ በቤተክርስቲያን እንዲያፈስ እንጸልያለን

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- ❖ **የጸሎት አገልግሎትን አስበን እንጸልያለን**

**ቀን - ቅዳሜ December 14, 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡- ታላቁ ተልዕኮ (ማቴዎስ 28:16-20)**

*አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ግን ኢየሱስ ወዳዘዛቸው ተራራ ወደ ገሊላ ሄዱ፥ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤ የተጠራጠሩ ግን ነበሩ። ኢየሱስም ቀረበና*

*እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፡- ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።*

*ማብራሪያ*

*ያዳነን ሊልከን ነው። እኛን ካወጣበት የጨለማ አገዛዝ ሌሎችን እንድናወጣ ነው ይህንም ተልእኮ መፈጸም እንድንችል*
*ቃሉን እና የመንፈስ ቅዱስን ሃይል እንዲሁም የሁልጊዜ አብሮነቱን ዋስትና አድርጎ ሰጥቶናል።*

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. *ታላቁን ተልእኮ ስናስብ*
    - *ለሰዎች መዳን ጌታ እንዴት ያለውን ዋጋ እንደከፈለና የሰውን ሁሉ መዳን እንደሚወድ እንመለከታለን፤በጌታ ዘንድ ለሰዎች መዳን ያለውን ልብ የእኛም ልብ እንዲሆንልን እንለምናለን።*
    - *የእግዚአብሔርን የድነት ወንጌል በምናወራበት ጊዜ ሁሉ ላኪው ከእኛ ጋር እንደሚሆን ተስፋ ስላለን ጌታን እያመሰገንን እንጸልያለን።*
    - *ይሔ እድል በጊዜ የተገደበ እንደሆነና በብዙ መቸኮል መደረግ እንዳለበት እያሰብን ጌታ ትኩረት አድርገን እንድናደርገው እንዲያነሳሳን እንጸልያለን*

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. *የቤተክርስቲያን ዋናው በምድር ላይ ያለችው ይህንን ተልእኮ ለማስፈጽም ነውና ፣ ህብረቶቻችን ሁሉ በዚህ ተልዕኮ የተቃኙ እንዲሆኑ እንጸልያለን።*
2. *ለቅዱሳን ሁሉ የተሰጠው ይህ ተልዕኮ በስተመጨርሻ ተጠያቂነትም እንዳለበት በማሰብ የዳነ ሰው የሚኖርበት ዋና አላማው ይህ እንደሆነ ባማወቅ እንዲሰማራ እንጸልያለን*

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

❖ **ግሎባል ሚሽን አስበን እንጸልያለን**

**ቀን - እሁድ December 15, 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡ -አምልኮ (መዝ63፡3-5)**

ምሕረትህ ከሕይወት ይሻላልና ከንፈሮቼ ያመሰግኑሃል።
እንዲህ በሕይወቴ ዘመን አመሰግንሃለሁ፥ በአንተም ስም እጆቼን አነሣለሁ።
ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚጠግቡ ትጠግባለች፥ ከንፈሮቼም ስምህን በደስታ ያመሰግናሉ።

**ማብራሪያ**

አምልኮ እግዚአብሔርን መውደድ፣ ማወደስ፣ ማክበር እና ማድነቅ ...እንደሆነና
ይልቁን ምህነቱን በጎነቱን ቸርነቱን ታላቁነቱን ሁሉን ቻይነቱን
ካየን ከኛ እርሱን ማምለክ በከንፈራችን ፍሬም ማወደስ እንደሚጠበቅ የዳዊት ህይወት ያስተምረናል

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. የሰማይና የምድር ፈጣሪ እግዚአብሔር እኛን የፈጠረን
    - እናመልከው ዘንድ ነውና የአንደበታችንን የምስጋና ፍሬ በፊቱ እናፈሳለን
    - አምልኮ እርሱን ማክበርና መውደድ ነውና በዚህ ህይወታችን የተሞላ እንዲሆን እንጸልያለን።
    - የአንደበት አምልኮ ከህይወት አምልኮ ጋር በቅዱሳን እይወት እንዳይለያይ እንጸልያለን።

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. ቤተክርስቲያን የአምልኮ ቦታ ነውና ጌታ የምናመልክበትን መንፈሱን እንዲያበዛ እንጸልያለን ።
2. በአምልኮ ጊዜ ጌታ በጉባዔው መካከል ሃይሉን እንዲያፈስ እንጸልያልን።
3. ለዳላስ ቤተክርስቲያን ጌታ ትላልቅ የመዝሙር ኮንሰርቶችን የምናድርግበት አቅምና ራዕይ እንዲሰጠን እንጸልያለን

ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት

- የዝማሬ አገልግሎትን አስበን እንጸልያለን

**ቀን - ሰኞ December 16, 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡- እግዚአብሄርን ማገልገል**

**እግዚአብሔርን በፍርሀት አገልግሉት፤ለእርሱ መራድም ደስ ያሰኛችሁ። መዝ2፡11**
**እግዚአብሔርን በደስታ አገልግሉት፤በፍሥሓ ዝማሬ ፊቱ ቅረቡ።(መዝ 100፡2)**

**ማብራሪያ**

**ታላቁን እና የተፈራውን አምላክ ሊያገለግሉ የሚችሉት ያዳናቸው ናቸው።**
**ስለሆነም በክርስቶስ ኢየሱስ የዳኑ ቅዱሳን ሁሉ እግዚአብሔረን ለማገልገል በታላቅ ደስታ እንዲሁም በፍርሃትና እና በአክብሮት መነሳሳት እንዳለባችው ቃሉ ይነግረናል።**

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. **ሌላው ያዳነን እንድናገለግለው ነውና ስለተሰጠን ይህ ታልቅ እድል ጌታን እያመሰገንን እንጸልያለን:**
2. **ልዑሉ እግዚአብሔርን ስናገለግል በሚያጋጥሙን መከራ ምክንያት በመማረር ሳይሆን በብዙ ደስታ ልናገለግለው እንዲገባ ቃሉ ይነግራናል።ለዚህም ልባችን በደስታ እንዲሞላ ምሬት እንዲወገድ እንጸልያለን**
3. **ጌታን የሚያገለግል እግዚአብሔርን በመፍራት ለእርሱ የሚገባውን ክብር በመስጠት ሊሆን ይገባልና ለቅዱሳን ሁሉ ይሔን እንለምናለን።**

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡**

1. **ጌታ በቤቱ እንዲያገለግሉ የጠራቸው አገልጋዮች አገልግሎታቸውን በብዙ ደስታና ያለምሬት መፈጸም እንዲችሉ እንጸልያለን።**
2. **የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ላይ የተሾሙትን አገልጋዮች በሙሉ እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ እንዲያገኛቸውና እንዲሁም በዚህ ጊዜ የሚታየው መስመር የለቀቀ አካሄድን የሚያቀኑበት ጥበብ እንዲሰጣቸው እንጸልያለን**

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- **የቤተሰብን አገልግሎት አስበን እንጸልያለን**

**ቀን - ማክሰኞ December 17, 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡- ለጋስነት**

ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና።ዕብ13፡16

**ማብራሪያ**

የእግዚአብሔር ልጆች የሆንበትን መንገድ ስናስብ በእግዚአብሔር ልጋስነት ነው።ይህም አንድያ ልጁን ስለኛ አሳልፎ በመስጠት የትገለጸ ነው። እኛም ልጆቹ ከእርሱ በተካፈልነው ባህርይ የተነሳ ለጋሶች መሆን እንዳለብን እናእግዚአብሔርንም ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት እንደሆነ ቃሉ ይነግረናል።

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. ከአምላካችን የተካፈልነው አንዱ ባህሪ ያለተገደበ ለጋስነቱን ነው። ይህን እያሰብን ማካፈል በልግስና እንዲበዛልን እንጸልያለን።
2. በልግስና ስናካፍል ሁልጊዜ
    - ልግስናን ማድረግ ጌታ ፍቅራችንን በተግባር እንድንገልጥ እድል እየሰጠን እንደሆነ እያሰብን እንድናደርገው  እንጸልያለን
    - እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትን መስዋህት በዚህ ውስጥ እንደሆነ አስበን እንድናደርገው ይህም እንዲበዛልን እንጸልያለን
    - ጌታ ቅዱሳንን  ከንፉግነትና ከራስ ተኮር ብቻ ከሆነ ህይወት እንዲጠብቀን እንጸልያለን።
    - ለሌላው ማካፈልን አቅም የሚያሳጣ የገንዘብ ፍቅር እንዲሰበር እንጸልያለን

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. ቤተክርስቲያን እንደተቋም ይህ የልግስና አገልግሎት እንዲበዛላት እንጸልያለን።
2. ሐዋርያቱ ፓውሎስን አንዱ ያሳሰቡን ድሆችን ችላ እንዳይል እንዲሁም ያዕቆብ በመልዕክቱ እናትና አባት የሌላቸውን ፣ ባልቴቶችን እንድናስብ ይነግረናል። በዚህ ስራ የበዛልን እንድንሆን እንደ ቤተክርስቲያን እንፀልያለን

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- **የዲያቆናት  አገልግሎት አስበን እንጸልያለን**

**ቀን - ረቡዕ December 18, 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡- ታላቁ ተስፋ(1ተሰ4፡ 13-18)**

*ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን።*

*ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና።በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፤እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን አንቀድምም፤ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥*

*ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።*

**ማብራሪያ**

*ሞት በዚህ ምድር ባሉ የሰው ልጆች መካከል ትልቅ የፍርሃት እና የሃዘን መንስኤ ነው፡፡ እኛ በክርስቶስ ትንሳኤ የምናምን ግን ከሞት ፍርሃት ነጻ ወጥተናል። ይልቁንም ከሞት ባሻገር ያለውን ፍጹም እረፍት ሰላም የሞላበት ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ሕይወት በተስፋ እንድንጠብቅ እንዲሁም በጌታ ሆነው ከዚህ አለም በሞት የተለዩትን(ያንቀላፉትን) ስናስብ ጌታ ሲምጣ አብረን እንደምናገኛቸው በማወቅ ሃዘናችን እንደሌሎች እንዳይሆን የእግዚሐብሔር ቃል ይመክረናል።*

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. *ህይወታችን በዚህ አለም ያለውንና የሚጠፋውን ብቻ ተስፋ በማድረግ የተመሰረተ ስላለሆነ ነገር ግን ጌታ ከሞት ባሻገር ባለው ህይወት ተስፋ ስለሰጠን እያመሰገንን እንጸልያለን*
2. *ሲሄድ ያዩት ጌታ እንዲሁ እየታየ ይመለሳል።የምንወደው አምላካችንና ጌታችን ይመጣል ።*
3. *ቀድመውን ከእኛ ዘንድ በሞት ስለሚለዩን ወገኖች ልናውቅ እና ልንጽናና የሚገባው ከጌታ ጋር አሁን እንደሆኑ እና ከእርሱ ጋር እንደሚመጡ ሲሆን፣ እርሱ ደግሞ ከሞት እንደተነሳ አንድ ቀን ከሞት በትንሳኤ ይነሳሉ።ይህንን በማሰብ እያመሰገንን እንጸልያለን።*

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. *ስለ ምጽዓቱ በመካከላችን ስብከቶች ፣ትምህርቶች እና ዝማሬዎች እንዲበዙ ጌታ ለባሪያዎቹ መልዕክትን እንዲያበዛላቸው እንጸልያለን።*
2. *እንዲሁም እናታቸውን ወይም አባታቸውን በሞት ላጡ ልጆች እግዚአብሔር በአባትነት ፍቅር ልባቸው እንዲደግፍ እንጸልያለን*

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- *የያንግ አደልትን አገልግሎት አስበን እንጸልያለን*

**ቀን - ሐሙስ December 19, 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡ - ስፍራ አዘጋጅቼላችኋለው(ዮሐ14፣ 1-3)**

**ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤ ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።**

**ማብራሪያ**

**ኢየሱስ በእርሱና በአባቱ ላይ ባለን እምነት ከጭንቀት ነጻ የሆነ ሕይወት እንድንኖር ነው የሚመክረን። የምናምነውም ኢየሱስ መጥቶ እንደሚወስደንና እርሱ ባለበት የምንኖርበትን ስፍራ እንደሚያዘጋጅልን ነው።**

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡**

1. ደቀመዛሙርቱ የጌታ እሄዳለው መልእክት ሲሰሙ ልባቸው ሲጨነቅ እንዳይታወኩ የሰጣቸው የማሳረፍያ ቃል
    - እምነት እንዲኖራቸው በአባቱም በእርሱም ያኔ ልባቸው ጭንቀት ያርፋል፡፡ጌታ እምነታችንን እንዳንጥል እንዲረዳን እንጸልያለን
    - የዘላለም መኖሪያች እርሱ ባለበት እንደሚሆን ማረጋገጫ የሰጠበት ነውና ጌታን እያመሰገንን እንጸልያለን
    - ጌታ የምሄደው ስፍራ ላዘጋጅላችሁ ነው ብሏል ፣ በጌታ ዘንድ ስለተዘጋጀልን መኖሪያ እያመሰገንን ልባችን በሰማይ ባለው ነገር ላይ እንድናደርግ እንጸልያለን።

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡**

1. የሚቀጥለውን ዓለም የሚናፍቅ ትውልድና ህብረት እንሆን ዘንድ ጌታ በቃሉ ልባችንን እንዲቃኝ እንጸልያለን
2. ቤተክርስቲያን መጥቶ ለሚወስደን ጌታ የተዘጋጁ ትውልድ የማዘጋጀት አላፊነት ከጌታ ተቀብላለችንና ይህን መወጣት እንድንችል እንጸልያለን

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- ❖ **የልጆች አገልግሎትን አስበን እንጸልያለን**

**ቀን - ዓርብ December 20, 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡ - አዲስ አካል (2ቆሮ5፡1-5)**

ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ፥ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንጻ እንዳለን እናውቃለንና። በዚህ ውስጥ በእውነት እንቃትታለንና፥ ከሰማይም የሚሆነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለንና
ለብሰን ራቁታችንን አንገኝም። በእውነትም የሚሞተው በሕይወት ይዋጥ ዘንድ ልንለብስ እንጂ ልንገፈፍ የማንወድ ስለ ሆነ፥ በድንኳኑ ያለን እኛ ከብዶን እንቃትታለን። ነገር ግን ለዚሁ የሠራን እግዚአብሔር ነው እርሱም የመንፈሱን መያዣ ሰጠን።

**ማብራሪያ**

አሁን የለበስነው ይህ አካል በድካም በበሽታ እንደሚጠቃ በመጨረሻም በሞት በመወገድ እንደሚበሰብስ እናውቃለን። ነገረ ግን ከነዚህ ሁሉ ነፃ የሆነና የተሻለ በሰማይ አዲስ አካል እንደምንለብስ መንፈሱንም የሰጠን ስለዚህ ዋስትና እንዲሆነን እንደሆነ ቃሉ ይነግረናል።

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ያለን ኑሮ እና የምንኖርበት አካል ማብቂያው እንዳለው ጊዜያዊ እንደሆነና የሰማዩ አካል ግን ዘላለማዊ እንደሆነ ይነግረናል። ለዚህም ታላቅ ተስፋ ጌታን እያመስገንን እንጸልያለን
2. አሁን በዚህ አካል የምንኖረው እይወት በመቃተት በናፍቆት የምኖረው ኑሮ ነውና አንድ ቀን ግን ከዚህ መቃተት እንደምንወጣ እርግጠኞች ያደረገን የተሰጠን የመንፈሱ መያዣ ነው። ጌታን እያመሰገንን እንጸልያለን።
3. በስጋቸው በተለያየ መከራ የሚያልፉትን በዚህ እወነት ልባቸው እንዲጽናና ጌታ እንዲረዳቸው እንጸልያለን።

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. የቅዱሳንን ልብ በሰማይ ያለውን ተስፋ ትኩር ብለው ተመልክተው የሚመላለሱ እንዲሆኑ ቤተክርስቲያን ይህን አይነት የተዘጋጁ ተስፋቸውን የሚያውቁ ህዝብ ለማዘጋጀት እንድትችል እንጸልያለን።

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- Youth ministry **አስበን እንጸልያለን**

**ቀን - ቅዳሜ December 21, 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡ - ንቅቶ መጠበቅ። (ማቴ24፡42-44)**

ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ። ያን ግን እወቁ፤ ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው ክፍል ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፥ በነቃ ቤቱም ሊቈፈር ባልተወም ነበር። ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና።

**ማብራሪያ**

የጌታ መምጫ ጊዜ መቃረብን የምናውቅባቸው ምልክቶች ምን እንደሆኑ በዝርዝር በመፅሐፍ ቅዱስ የተገለጠልን ቢሆንም የሚመጣበትን ቀን በተመለከተ ግን ስለማናውቅ ሁል ጊዜ ዝግጁዎች እንድንሆን ቃሉ በማስጠንቀቅ ይመክረናል።

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. የጌታ መምጣት
   - እንደሰነፎች ሳይሆን ለእኛ ለምናምን እርግጥ ነው። አመጣጡ ግን በማናስብበት ጊዜ ድንገት ስለሆነ ጌታ በማስተዋል እንድንኖር እንዲረዳን እንጸልያለን
   - ደግሞ ድጋግሞ ንቁ እያለ ይመክረናል ፣በዚህ ዘመን ሰዎችን መንፈሳዊ እንቅልፍ ውስጥ የሚያስገባ ዘምነ እንደአላቸው በማስብ እንዲኖሩ የሚያደርግ የክፉ ውሸት የሰውን ልብ እያሳተ አለና ጌታ ብዙዎችችንን ከእንቅል እንዲያነቃን እንጸልያለን
   - በሰማይ ቤት እንዳለውና እንደሚሄድ ሰው የተዘጋጀን ለሌላውም ወንጌል የምናካፈል እንድንሆን እንጸልያለን

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. እግዚአብሔር የቤተክርስቲያናችንን ጩኸት ሊመጣ ነው በሚል እንዲሞላ እንጸልያለን
2. በቴክሳስ እና በአሜሪካ ያሉት የኢትዮጵያና የኤርትራዊያን ቅዱሳን ለመጨረሻው ሊመጣ ነው ጥሪ በህብረት መስራት እንዲችሉ እንጸልያለን

**ለአገልግሎት ክፍል ጸሎት**

- ❖ የሚዲያን አገልግሎት አስበን እንጸልያለን

**ቀን - እሁድ December 22, 2024**

**የዕለቱ ንባብ፡ - ምስጋና(መዝ28፡6-7)**

የልመናዬን ቃል ሰምቶኛልና እግዚአብሔር ይመስገን።እግዚአብሔር ኃይሌና ጋሻዬ ነው፤ ልቤ በእርሱ ታመነ እኔም ተረዳሁ፤ሥጋዬም ደስ ይለዋል፥ ፈቅጄም አመሰግነዋለሁ።

**ማብራሪያ**

ዳዊት እግዚአብሄር ልመናዬን (ጸሎቴን)ሰምቶኛል ብሎ ያመሰግናል።ጌታ በሚፈልገው ሰዓት እንደሚደርሰለት ስላየው ሃይሌ ጋሻዬ እያለ በእርሱ መደሰቱን እየገለጸ በፈቃዱም ምስጋናን ያቀርባል።

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡ -**

1. እግዚአብሔር ጸሎትን የሚሰማ ነውና በእነኚህ ቀናት ጸሎታችንን ስለሰማን እያመሰገንን እንጸልያለን
2. በፊታችን በሚኖሩት ዘመናት ልክ እንደትናንትናው ጌታ አምላካችንን ሃይልና ጋሻችን ነው እያልን እያወጅን እንጸልያለን

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡ -**

1. እግዚአብሔር በእነኙህ ዘመናት ሁሉ ባለንባት አጥቢያ ስላደርገው መልካምነት እያስተዋልን በምስጋና በፊቱ እንቀርባለን
2. እንዲሁ የእግዚአብሔር አብሮነት በፊታችን ባሉት ዓመታት ላይ በቤተሰብ ፤በቤተክርስቲያንና በምድራችን ላይ እንዲሆን እንጸልያለን(መዝ91፡14)

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2-Dec | ሉቃስ1-2 | | 9-Dec | ሉቃስ 10 | | 16-Dec | ሉቃስ 18 | |
| 3-Dec | ሉቃስ 3-4 | | 10-Dec | ሉቃስ 11 | | 17-Dec | ሉቃስ 19 | |
| 4-Dec | ሉቃስ 5 | | 11-Dec | ሉቃስ 12 | | 18-Dec | ሉቃስ 20 | |
| 5-Dec | ሉቃስ 6 | | 12-Dec | ሉቃስ 13 | | 19-Dec | ሉቃስ 21 | |
| 6-Dec | ሉቃስ 7 | | 13-Dec | ሉቃስ 14 | | 20-Dec | ሉቃስ 22 | |
| 7-Dec | ሉቃስ 8 | | 14-Dec | ሉቃስ 15-16 | | 21-Dec | ሉቃስ 23 | |
| 8-Dec | ሉቃስ 9 | | 15-Dec | ሉቃስ 17 | | 22-Dec | ሉቃስ 24 | |

ማስታወሻ መያዣ



“እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፥ ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን” (ኤፌ 3፡20-21) ።